girl scouts nation's capital

# የአዲስ መሪ የመመሪያ መጽሔት

2024-2025








# እንኳን ደህና መጡ!



በ Girl Scouts Nation's Capital ውስጥ በጎ ፈቃደኛ የቡድን መሪ ሆነው ለመስራት ስለፈቀዱ እናመሰግናለን!

ዓለምን የተሻለች ቦታ የሚያደርጉ፣ ወኔ፣ በራስ መተማመን እና መልካም ስነ-ምግባር ያላቸው ሴት ልጆችን መገንባት የተቻለው አስደናቂ ተሞክሮዎችን ለመፍጠር እንደ እርስዎ 'አዎን' በሚሉ በሺዎች የሚቆጠሩ በጎ ፈቃደኞች ምክንያት ነው።

ይህ መመሪያ እንደ አዲስ የቡድን መሪ ለሚያሳልፏቸው የመጀመሪያዎቹ ሶስት ወራት􀀀የመስመር ላይ (ኦንላይን) የስልጠና ፖርታል ከመጠቀም ጀምሮ፣ የመጀመሪያው የቡድን ስብሰባዎን በማስኬድ ዙሪያ እና በመካከል በሚኖርዎት ቆይታ ወቅት በሌሎችም መንገዶች ያግዝዎታል።

# እሴቶቻችን፡ የ Girl Scout ቃል ኪዳን እና ህግ

## የ Girl Scout ቃል ኪዳን፡

*የሚከተሉትን ለማድረግ እንደምሞክር፣ ቃሌን እሰጣለሁ፡*
*ፈጣሪን እና ሀገሬን ለማገልገል፣*
*ሰዎችን ሁል ጊዜ ለመርዳት፣*
*እንዲሁም በ Girl Scout ህግ ለመተዳደር።*

**የ Girl Scout ን ቃል-ኪዳን ሲገቡ፣ እያንዳንዱ አባላት "ፈጣሪ" የሚለውን ቃል ከራሳቸው መንፈሳዊ እምነት ጋር በሚስማማ ቃል መተካት ይችላሉ።*

## የ Girl Scout ህግ፡

*የሚከተሉትን ለመሆን የተቻለኝን አደርጋለሁ*
*ሐቀኛ እና ፍትሃዊ፣*
*ተግባቢ እና ተባባሪ፣*
*በጎ እና አሳቢ፣*
*ደፋር እና ጠንካራ፣ እንዲሁም*
*ለምናገረው እና ለማደርገው ኃላፊነት የሚሰማኝ*
*እንዲሁም እራሴን እና ሌሎችን ለማክበር፣*
*የበላይ አስተዳደርን ለማክበር፣ግብዓቶችን በአግባቡ ለመጠቀም፣*
*ዓለምን የተሻለ ቦታ ለማድረግ እንዲሁም*
*ለእያንዳንዱ Girl Scout እህት ለመሆን።*




ከ **110 ዓመታት** በላይ

Girl Scouts አለምን የተሻለች ቦታ የሚያደርጉ ደፋር፣ በራስ መተማመን ያላቸው እና ጠንካራ ምግባርን የተላበሱ ሴቶችን እየገነባ ነው።

| | ማውጫ | ገጽ |
|---|---|---|
| | የቡድን መሪ የአቅጣጫ ካርታ | 4 እና 5 |
| **አንደኛ ሳምንት:** | ምዝገባ እና የኋላ ታሪክ ማጣሪያ | 6 |
| | gsLearn መሳሪያን መጠቀም: መጀመር | 6 |
| | የ gsLearn ትምህርት: የቡድን መሪነት ጉዞዎን መጀመር | 7 |
| | New Leader Rally ን ይቀላቀሉ | 8 |
| | ለ Girl Scouts Essentials Box (ዴይዚ) መመዝገብ | 8 |
| | MyGS ውስጥ የቡድን ዝርዝር መግለጫ እና የበጎ ፈቃደኞች መገልገያ ስብስብን ማገኘት | 9 |
| **ሁለተኛ ሳምንት:** | ከአጋር መሪ ጋር መገናኘት | 10 |
| | ከአገልግሎት ክፍል የእንግዳ አቀባበል ባለሙያ ጋር መገናኘት | 11 |
| | በመጀመሪያው የአገልግሎት ክፍል ስብሰባ ላይ መገኘት | 11 |
| | የ gsLearn ትምህርት: የተንከባካቢ ተሳትፎ | 12 |
| | ለአሳዳጊዎች ስብሰባ መርሐግብር ማስያዝ | 13 |
| | ቤተሰቦችን ለማግኘት የቡድን ዝርዝር መግለጫን መጠቀም | 13 |
| **ሦስተኛ ሳምንት:** | የአሳዳጊዎች ስብሰባን ማዘጋጀት | 14 |
| | የ gsLearn ትምህርት: የቡድን መሪ መመሪያዎች | 15 |
| | ከእርሶ የሰራተኛ አባልነት ባለሙያ ጋር መገናኘት | 15 |
| **አራተኛ ሳምንት:** | የ gsLearn ትምህርት: የቡድን ገንዘብ አስተዳደር | 16 |
| | የቡድን ገንዘብ አስተዳዳሪን ከአገልግሎት ክፍል ገንዘብ አስተዳዳሪ ጋር ማገናኘት | 16 |
| | ለመጀመሪያው የቡድን ስብሰባ መርሐግብር ማውጣት | 17 |
| | ታላቅ የቡድን ስብሰባ ማቀድ | 17 |
| **ስድስተኛ ሳምንት:** | የመጀመሪያውን የቡድን ስብሰባ ማድረግ | 18 |
| | ለአዲስ መሪ የተዘጋጁ ትምህርታዊ ጉባኤዎችን ኦንላይን ላይ መመልከት | 18 |
| | የቡድን ማህደር ዝመናን ማጠናቀቅ | 18 |
| | የ gsLearn ትምህርት: በፕሮግራም ደረጃ የሚያስፈልጉ መሰረታዊ ነገሮች | 18 |
| **ስምንተኛ ሳምንት** | ለቡድን የባንክ ሂሳብ መክፈት | 19 |
| | gsLearn: በፕሮግራም ደረጃ ለሚዘጋጅ የቀጥታ ስርጭት ክፍለ ጊዜ መመዝገብ | 19 |
| | gsLearn: DEIA እና አካታችነት{ | 19 |
| **3ኛ ወር** | በፕሮግራም ደረጃ የሚዘጋጅ የቀጥታ ስርጭት ስልጠና ክፍለ ጊዜ ላይ መገኘት | 24 |
| **አባሪ** | ማለም፣ ሰርቶ ማግኘት፣ ማድረግ ስራ ፈጣሪነት | 20 |
| | ተጨማሪ መርጃዎች | 21 |
| | ስለ ቡድን የገንዘብ አያያዝ መታወቅ ያለባቸው ሰባት ታላላቅ ነገሮች | 22 |
| | በወጣቶች የሚመራ በጀት የማውጣት ክህሎት | 23 |

*ወደ Girl Scouts Nation's Capital እንኳን በደህና መጡ! ይህ ወደ ስኬት የሚወስድዎ የቡድን መሪነት የአቅጣጫ መመሪያዎ ነው!ይህ የአቅጣጫ መመሪያ በ Girl Scout ውስጥ በሚኖርዎት አመት ላሉት የመጀመሪያዎቹ 3 ወራት በአጋዥነት ያገለግልዎታል!*

## 1ኛ ሳምንት

- [ ] ተግባር፡ የኋላ ታሪክ ማረጋገጫን ማጠናቀቅ
- [ ] ተግባር፡ gsLearn መሳሪያን መጠቀም
- [ ] ተግባር፡ New Leader Rally ን ይቀላቀሉ
- [ ] ተግባር፡ ለ Girl Scouts Experience Box መመዝገብ (አዲስ የዴይዚ መሪ ከሆኑ )
- [ ] ተግባር፡ የቡድኖች ዝርዝር መግለጫ እና የበጎ ፈቃደኞች መገልገያ ስብስብን MyGS ውስጥ ማግኘት*
- [ ] የ gsLearn ትምህርት፡ የቡድን መሪነት ጉዞዎን መጀመር

## ማብራሪያ

የ gsLearn ትምህርት፡ ለቡድን መሪ የሚያስፈልግ ስልጠና

ተግባር: በቡድን መሪ የሚጠናቀቅ ተግባር

ስብሰባ : የሚሳተፉባቸው ወይም የሚመሯቸው ስብሰባዎች

የምክር ቤት ሰራተኞች፡ የምክር ቤት ሰራተኛ አባል ያሉበትን ሁኔታ ለማረጋገጥ ሊያገኝዎት ይችላል

*የኮከብ ምልክት ያላቸው*: በየ Girl Scout አመቱ መጠናቀቅ አለባቸው*

## 2ኛ ሳምንት

- [ ] ተግባር፡ የተንከባካቢ ተሳትፎ ትምህርቱን ካጠናቀቁ በኋላ የሚካሄድ የተንከባካቢ ስብሰባን ማቀድ*
- [ ] ተግባር፡ ወደ ቡድኑ የሚቀላቀሉ ቤተሰቦችን ለማግኘት እና ስለአሳዳጊዎች ስብሰባ ለማሳወቅ የቡድን ዝርዝር መግለጫን ይጠቀሙ*
- [ ] የ gsLearn ትምህርት፡ የተንከባካቢ ተሳትፎ
- [ ] ስብሰባ: ከአጋር መሪ ጋር መገናኘት*
- [ ] ስብሰባ: ከአገልግሎት ክፍል የእንግዳ አቀባበል ባለሙያ ጋር የአቀባበል ክፍለ ጊዜ ላይ መገኘት (ዝግጅቱ ሲኖር ያሳውቁዎታል)
- [ ] ስብሰባ: በመጀመሪያው የአገልግሎት ክፍል ስብሰባ ላይ መገኘት

## 6ኛ ሳምንት

- [ ] ተግባር፡ የመጀመሪያውን የቡድን ስብሰባ ማድረግ
- [ ] ተግባር፡ ለአዲስ መሪ የተዘጋጁ ትምህርታዊ ጉባኤዎችን ኦንላይን ላይ መመልከት
- [ ] ተግባር፡ የቡድን ማህደር ማዘመኛ ቅጽን ማጠናቀቅ
- [ ] የ gsLearn ትምህርት፡ በፕሮግራም ደረጃ የሚያስፈልጉ መሰረታዊ ነገሮች (ማለትም፡ የዴይዚ መሰረታዊ ነገሮች፣ የታዳጊ ወጣቶች አማካሪዎች ክህሎቶች)

በተሞክሮዎ መካከል ማናቸውም ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎን የአገልግሎት ክፍል ቡድንዎን ወይም የ Girl Scouts Nation‘s Capital ሰራተኞችን በኢሜይል (customercare@gscnc.org) ያግኙ።

## 3ኛ ሳምንት

- ☐ የ gsLearn ትምህርት፡ የቡድን መሪ መመሪያዎች
- ☐ ስብሰባ፡ የአሳዳጊዎች ስብሰባን ማዘጋጀት
  - ☐ ተግባር፡ የ Girl Scout የጤና መዝገብ ቅጾችን እና Meet My Girl Scout (Girl Scout ልጄን ይተዋወቁ) ቅጾችን መሰብሰብ*
  - ☐ ተግባር፡ ለቡድን ኮሚቴ የሚያገለግሉ በጎ ፈቃደኞችን ይለዩ
- ☐ የምክር ቤት ሰራተኞች፡ ከሰራተኛ አባልነት ባለሙያ ጋር ይገናኙ (ይደውልሎታል!)

## 4ኛ ሳምንት

- ☐ ተግባር፡ የቡድን ገንዘብ አስተዳዳሪን ከአገልግሎት ክፍል ገንዘብ አስተዳዳሪ ጋር ማገናኘት
- ☐ ተግባር፡ ለመጀመሪያው የቡድን ስብሰባ መርሐግብር ማውጣት*
- ☐ የ gsLearn ትምህርት፡ የቡድን ገንዘብ አስተዳደር
- ☐ የ gsLearn ትምህርት፡ የቡድን መሪ መመሪያዎች (አማራጭ ትምህርቶች)

## 8ኛ ሳምንት

- ☐ ተግባር፡ የቡድን አስተዳዳሪው የቡድኑን የባንክ ሂሳብ በሚከፍቱበት፣ ተቀባይነት ያለውን የሂሳብ ፈራሚ በሚለዩበት እና ከባንክ ደብዳቤ በሚያገኙበት ወቅት ድጋፍ ማድረግ
- ☐ የ gsLearn ትምህርት፡ ለቀጥታ ስርጭት መመዝገብ (ማለትም፡ የዴይዚ የቀጥታ ስርጭት ክፍለ-ጊዜ፣ የታዳጊ ወጣቶች አማካሪዎች የሚያስፈልጓቸው ክህሎቶች ክፍለ-ጊዜ)
- ☐ የ gsLearn ትምህርት፡ DEIA ላይ ቁርጠኝነት እና አካታች ቋንቋ

## 3ኛ ወር

- ☐ ተግባር፡ የቀጥታ ስርጭት ክፍለ-ጊዜ ላይ በ Zoom ወይም በአካል መገኘት (ማለትም፡ የዴይዚ የቀጥታ ስርጭት ክፍለ-ጊዜ፣ የታዳጊ ወጣቶች አማካሪዎች የሚያስፈልጓቸው ክህሎቶች ክፍለ-ጊዜ)



## አንደኛ ሳምንት

# ተግባር፡ የኋላ ታሪክ ማረጋገጫን ማጠናቀቅ

ለ Girl Scouts Nation's Capital አባልነት መመዝገብ እንደሚያስፈልግ ሁሉ የኋላ ታሪክ ማረጋገጫን ማጠናቀቅ ያስፈልጋል። ለበጎ ፈቃደኝነት ሚና ከተመዘገቡ በኋላ የኋላ ታሪክ ማረጋገጫው ይጠየቃል፡፡

## እንደ በጎ ፈቃደኛ ለመመዝገብ ቅደም ተከተሎች፡


1. ወደ www.mygs.girlscouts.org ይሂዱ
2. የኃላፊነት ሚናን በዚፕ ኮድ ወይም ሀገር፣ ግዛት እና ከተማ እንዲሁም በቡድን ቁጥር ይፈልጉ፤ አስፈላጊ ከሆነ ተጨማሪ ማጣሪያዎችን ይጠቀሙ
3. በትክክለኛው ቡድን ውስጥ ትክክለኛ ሚና ለማግኘት 'ሚና አክል' የሚለውን ይጫኑ
4. መለያዎን ለመፍጠር ወይም ቀድሞ ወደነበርዎት መለያ ለመግባት **ግባ** የሚለውን ይጫኑ የሚፈለገውን መረጃ ለማስገባት እና ለአባልነት (25 ዶላር) ለመክፈል ወይም የገንዘብ እገዛን ለመጠየቅ ቀጥለው የሚታዩትን ስክሪኖች በመጠቀም ይቀጥሉ
5. የመግቢያ መረጃዎን ያስቀምጡ! gsLearn እና Volunteer Toolkit (የበጎ ፈቃደኞች መገልገያ ስብስብን) ጨምሮ My GS ውስጥ ለመግባት የመግቢያ መረጃዎን ይጠቀማሉ።
6. የኋላ ታሪክ ማጣሪያን ለማስገባት ከ advocates@sterlingvolunteers.com የኢሜይል መጥሪያ ይቀበሉ። የኋላ ታሪክ ማጣሪያ ክፍያ $8.50 ; ሲሆን ለሚፈልጉ የገንዘብ እገዛ አለ።


# ተግባር፡ gsLearn መሳሪያን መጠቀም

አሁን በበጎ ፈቃደኝነት የተመዘገቡ በመሆኑ፣ ስልጠና ለመጀመር gsLearn መሳሪያን መጠቀም ይችላሉ።

## gsLearn መሳሪያን ለመጠቀም፡

1. ወደ www.gscnc.org ይሂዱ
2. እዚህ ላይ ጠቅ ያርጉ **MYGS**
3. ወደ MY GS መለያዎ ይግቡ
4. በግራ የጎን ዝርዝር ላይ gsLearn የሚለውን ይጫኑ።




ይህ የእርስዎ የዋና እይታ ገጽ ነው። የጀመሯቸውን፣ ሳያልቁ የዘገዩ እና የተጠናቀቁ የትምህርት ጉዞዎችን እዚህ ላይ ማየት ይችላሉ። መረጃውን ዳግም ለመመልከት ከፈለጉ ያጠናቀቁትን ማንኛውንም የትምህርት ጉዞ ወይም ሞጁል እንደገና መውሰድ ይችላሉ።

በዋና ገጽዎ ላይ ለተለያዩ የፕሮግራም ደረጃዎች (ዴይዚ፣ ብራውኒ፣ ወዘተ) በርካታ የስልጠና ትምህርቶችን ይመለከታሉ። ለእርስዎ ደረጃ የሚሆን አንዱን ፈልገው ያግኙና ለመጀመር እሱን ይጫኑ!



**አንደኛ ሳምንት**

# የ gsLearn ትምህርት፡ : የቡድን መሪነት ጉዞዎን መጀመር


ስልጠና የሚያስፈልግ ሲሆን፣ ነፃ እና ሙሉ በሙሉ በመስመር ላይ ሊከናወን የሚችል ነው! ስልጠናው፣ በ Girl Scout ውስጥ ወጣት አባላት ምርጥ ተሞክሮ እንዲኖራቸው ለማስቻል በጎ ፈቃደኞች የሚያስፈልጓቸውን ክህሎቶች እና መሳሪያዎች ይሰጣል።

ከአገልግሎት ክፍልዎ እንግዳ አቀባበል ባለሙያ ጋር የሚኖርዎት ክፍለ-ጊዜ የስልጠና መስፈርቶችን እንዲሁም የአካባቢዎን የአገልግሎት ክፍል የስራ ሂደት ለመገንዘብ ይረዳዎታል።

ለቡድን መሪዎች አስፈላጊ ስልጠና፡

- 204 የቡድን መሪነት ጉዞዎን መጀመር፣ 204 የተንከባካቢ ተሳትፎ፣ የዘዴ ትምህርቶች
- በፕሮግራም ደረጃ መሰረታዊ ነገሮች (ማለትም ፣ የዴይዚ መሰረታዊ ነገሮች፣ የብራውኒ መሰረታዊ ነገሮች፣ወዘተ) በራስ መርሃ-ግብር የሚወሰዱ
- በፕሮግራም ደረጃ <u>የቀጥታ</u> ክፍለ-ጊዜ
- የቡድን ገንዘብ አስተዳደር
- DEIA ላይ ቁርጠኝነት እና አካታች ቋንቋ

## Troop Leaders need to complete training within 3 months of appointment. Plan ahead – train-


2020 Upcoming Courses
File Edit View Tools Help
Request edit ac

| | | | |
|---|---|---|---|
| 10/18 & 11/07-11/08 | 2:00 PM & 9:00 AM | Lightweight Camping (Planning Session and Overnight) | Camp Brighton Woods |

**Troop Leaders - Log into gsLearn to start your training!**

Program basics training listed below is the required live interactive training for a troop leader. Each level has an online component as well that must be completed prior to the live training on gsLearn. More info on gsLearn can be found here.

| Date | Time | Course | Address |
|---|---|---|---|
| 8/11 | 11:00 AM | Skills for Teen Advisors (Arabic and English) | Virtual |
| 9/09 | 6:00 PM | Daisy Basics | Virtual |
| 9/10 | 6:30 PM | Brownie Basics | Virtual |
| 9/12 | 9:00 AM | Junior Basics | Camp Brighton Woods |
| 9/12 | 1:00 PM | Junior Basics | Camp Brighton Woods |
| 9/12 | 1:00 PM | Daisy Basics | Camp Brighton Woods |
| 9/12 | 1:00 PM | Brownie Basics | Camp Brighton Woods |
| 9/13 | 9:00 AM | Skills for Teen Advisors | Camp Brighton Woods |
| 9/13 | 1:00 PM | Junior Basics | Camp Brighton Woods |
| 9/14 | 6:30 PM | Junior Basics | Virtual |
| 9/19 | 10:00 AM | Brownie Basics | Virtual |
| 9/19 | 2:30 PM | Junior Basics | Virtual |
| 9/20 | 6:30 PM | Brownie Basics | Virtual |

gsLearn ውስጥ በቀጥታ ስርጭት የሚከናወኑ ስልጠናዎች፣ የሚካሄዱት በምናባዊ መንገድም ሆነ በአካል፣ የቀጥታ ክፍለ-ጊዜ ብለን እንጠራቸዋለን። በፕሮግራም መሰረታዊ የትምህርት ጉዞ ማጠቃለያ ላይ፣ ይህ ስክሪን በቀኝ በኩል ይታያል፣ ይህም የትምህርት ጉዞውን ለመጨረስ የሚያስፈልጉትን ሁሉንም መጪ የቀጥታ ክፍለ-ጊዜዎች ያሳያል።

መጪውን የዴይዚ/ብራውኒ/ጁኒየር፣ ወይም ከቤት ውጪ የምግብ ዝግጅት እና ከቤት ውጪ ቆይታ የቀጥታ ክፍለ-ጊዜዎችን ዝርዝር ለማግኘት ጥሩው ቦታ የመጪ ትምህርቶች ሰነድ ሲሆን በ **www.gscnc.org -> ላይ በጎ ፈቃደኝነት -> አስፈላጊ ስልጠና -> መጪ ትምህርቶች ላይ ይገኛል።**

ተጨማሪ ስልጠናዎች በየወሩ ሊጨመሩ ይችላሉ፣ በተለይም በወሩ 3ኛው ወይም 4ኛው ሳምንት ላይ። ይህ ትምህርት ለበጎ ፈቃደኞች እና ለ Girl Scouts ጥቅም ሲባል የተዘጋጀ መሆኑን ያስታውሱ። ተሳትፎ ግዴታ ነው።


**አዲስ በጎ ፈቃደኞች ሁሉንም በራስ መርሃ-ግብር እና በቀጥታ ክፍለ-ጊዜዎች የሚወሰዱትን ጨምሮ የሚጠየቀውን ስልጠና ለመጨረስ የ 3 ወራት ጊዜ አላቸው።**

**ይህን ያውቁ ኖሯል!**
አንዳንድ ተግባራት ልዩ ስልጠና ያስፈልጋቸዋል፡፡ ለምሳሌ፣ካምፕ ፋየር ለማዘጋጀት በጎ ፈቃደኞች 204 S'mores & Fire Safety፣ አልያም 204 Campout & Cookout ስልጠናን ማጠናቀቅ አለባቸው፡፡ ስለ ልዩ ተግባራት የስልጠና መስፈርቶች የበለጠ መረጃ ለማግኘት የበጎ ፈቃደኞች መሰረታዊ መመሪያዎችን ይመልከቱ።

# አንደኛ ሳምንት

## ተግባር፡ New Leader Rally ን ይቀላቀሉ

አዲስ መሪዎች የእኛን New Leader Rally እንዲቀላቀሉ ተጋብዘዋል! ይህ ስብሰባ ጥያቄዎችን ለመጠየቅ እና ከምክር ቤት ሰራተኞች ድጋፍ ለማግኘት አስተማማኝ ቦታ ነው። ከእያንዳንዱ የአዲስ መሪ ትምህርታዊ ጉባኤ የተወሰዱ ቅጂዎች እና ተንቀሳቃሽ ይዘቶችን እንለጥፋለን።




የመቀላቀያ ጥያቄ ለማቅረብ ይህንን አገናኝ ይጎብኙ፦
https://rallyhood.com/68390/messages

**Rallyhood.com፣** Rallies (ራሊስ) የሚባሉ ልዩ ቡድኖች ያሉት መድረክ ነው። እርስዎ አባል መሆን ሊፈልጉባቸው የሚችሏቸውን የ Rallies ዝርዝር ለማግኘት፣ የ GSCNC ድር ጣቢያን ይመልከቱ።
ሁሉም የቡድን መሪዎች ለፕሮግራማቸው ደረጃ የሚመጥን ስብሰባን - DBJ ወይም Teen እንዲቀላቀሉ እንመክራለን።

በተጨማሪም Rallyhood ከቡድንዎ፣ ከአገልግሎት ክፍልዎ ወይም ከሌላ ቡድን ጋር መረጃ ለመለዋወጥ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል። መልዕክቶችን መለጠፍ፣ ዝግጅቶችን ማከል እና ሌሎችንም ማድረግ ይችላሉ! Rallyhoodን በስልክ መጠቀም ቀላል የሚያደርግ የ Rallyhood የስልክ መተግበሪያ አለ። **ስለ Rallyhood የበለጠ ለመረዳት፣ gsLearn ትምህርት ላይ "የ Rallyhood አጠቃቀም" የሚለውን ይመልከቱ፡፡**

## ተግባር፡ ለ Girl Scout Experience Box መመዝገብ*

**ለአዲስ የዴይዚ ቡድን መሪዎች ብቻ*

The Girl Scout Experience Box ለመጀመሪያ አመት Girl Scout ዴይዚ ቡድኖች ድንቅ መርጃ የሚያቀርብ አዲስ ፕሮግራም ነው። ከኦገስት 2024 ጀምሮ፣ አዲስ የዴይዚ ቡድን፣ ደረጃ በደረጃ መመሪያዎች፣ የተሟሉ አቅርቦቶች እና አበረታች ምክሮችን የያዘ ወርሃዊ የአቅርቦት ሳጥን ይደርሰዋል። ይህ በነጻ የሚቀርብ ተጨማሪ መርጃ፣ የዴይዚ የመጀመሪያ አመት ቡድኖችን እቅድ በመከተል በቀጥታ ለቡድን መሪዎች ይደርሳል።




ይህ በ2024/2025 የትምህርት ዘመን ወደ አጸደ ህጻናት እና/ወይም አንደኛ ክፍል የሚገቡ እና ለመጀመሪያ ጊዜ አብረው የሚሳተፉ Girl Scoutsን ላካተቱ አዲስ ዴይዚ ቡድኖች የሚተገበር ነው። የመጀመሪያውን ሳጥን ለመቀበል፣ እያንዳንዱ አዲስ የዴይዚ ቡድን የሚከተሉትን ማድረግ አለበት፡ ቢያንስ አራት አዳዲስ ዴይዚ Girl Scouts እና የኋላ ታሪክ ማጣሪያ በሚያስፈልገው ኃላፊነት ላይ አራት አዋቂ በጎ ፈቃደኞችን መመዝገብ፤ እና አስፈላጊውን የትዕዛዝ ቅጽ መሙላት ይኖርበታል፡፡


የብቁነት መስፈርቶችን ሲያሟሉ ከእኛ ማሳወቂያ ይደርስዎታል - ይፋዊ ጥያቄ ለማቅረብ ቅጹን መሙላትዎን ያረጋግጡ! ከእኛ ማሳወቂያ አልደረስዎትም? membershipsupport@gscnc.org ላይ ያግኙን።

# አንደኛ ሳምንት

**ተግባር፡ የቡድኖች ዝርዝር መግለጫ እና Volunteer Toolkit (የበጎ ፈቃደኞች የመገልገያ ስብስብ) በ MyGS ውስጥ ያግኙ**

gsLearn ላይ 204 Getting Started as a Troop Leader (204 የቡድን መሪነት ጉዞዎን መጀመር) ካጠናቀቁ፣ ይህ ለእርስዎ አዲስ አይሆንም።


የበጎ ፈቃደኞች መገልገያ ስብስብ (VTK) እያንዳንዷ Girl Scout የመሪነት፣ የስኬት እና የጀብዱ ህይወት የመገንባት እድል ያላት መሆኑን የ Girl Scout የአመራር ተሞክሮን በመስጠት ማረጋገጥ እንዲችሉ በጎ ፈቃደኞችን የሚደግፍ ዲጂታል መርጃ ነው። በጎ ፈቃደኞች፣ የሚደገፍ ነገር ግን በሴት ልጅ የሚመራ ፕሮግራም እንዲያቅዱ እና እንዲተገብሩ የሚያስችሉ ግብዓቶች አሉት። በተጨማሪም ቤተሰቦች የቡድኑን መርሃ-ግብር ለማየት የበጎ ፈቃደኞች የመገልገያ ስብስብን መጠቀም፣ እንዲሁም በመርጃዎች ክፍል ውስጥ የደንብ ልብስ መመሪያዎችን፣ የ Girl Scout ቤተሰብ መመሪያ መጽሔት እና በፕሮግራማቸው ደረጃ መሰረት ሁሉንም ወቅታዊ የእውቅና አርማዎች እና ሽልማቶች፣ እና ሌሎች ሌሎችንም ማግኘት ይችላሉ።




ወደ የበጎ ፈቃደኞች መገልገያ ስብስብ በመሄድ እና 'የእኔ ቡድን' የሚለውን ትር በመጫን የቡድንዎን ዝርዝር መግለጫ ያግኙ።

**የበጎ ፈቃደኞች መገልገያ ስብስብ ተግባራት፡**

- በቡድን መሪዎች የሚተዳደር ሲሆን ቤተሰቦች መጠቀም እና ማየት ይችላሉ!
- የቡድኑን አመት ለማቀድ የቀን መቁጠሪያ መሳሪያ
- የእውቅና አርማዎች እና የጉዞዎች መመሪያዎች፣ እንዲሁም ሙሉ አመቱን የሚያሳትፉ የትግበራ ፕሮጀክቶች
- የሁሉም ወቅታዊ አባላት ዝርዝር መግለጫ ከመገኛ መረጃዎቻቸው ጋር
- የ Girl Scout ተሳትፎ እና ስኬቶች ክትትል
- የመገናኛ መሳሪያ - የስብሰባ ማስታወሻዎችን ኢሜይል ማድረግ፣ ሰነዶችን ማያያዝ እና ሌሎችም!
- የደህንነት እንቅስቃሴ ፍተሻዎች፣ የበጎ ፈቃደኞች መሰረታዊ መመሪያዎች እና ሌሎች ህትመቶችን የመሳሰሉ ለሁሉም Girl Scout ቤተሰቦች የሚሆኑ መርጃዎች



# ሁለተኛ ሳምንት

## ስብሰባ፡ ከአጋር መሪ ጋር መገናኘት


**የቡድን መሪዎች በአንድነት፡**

- Girl Scouts የመፍጠር እና ወኔ ያለው መሪ የመሆን አቅማቸው ላይ እንዲደርሱ ያግዛሉ
- Girl Scouts የመውደቅ ፍራቻ ሳያድርባቸው አዳዲስ ነገሮችን የሚሞክሩበት ምቹ ቦታን ይፈጥራሉ
- Girl Scouts ለሚቀጥሉት አሥርት ዓመታት የሚጠቀሙባቸውን ትምህርቶች ይሰጣሉ
- ከቡደኖቻቸው ጋር በመሆን አዳዲስ ነገሮችን ይሞክራሉ
- መሪዎች የራሳቸውን የአደረጃጀት እና የአመራር ችሎታ ያዳብራሉ
- አለም አቀፋዊ የእህትማማችነት ማህበረሰብን ይቀላቀላሉ
- Girl Scouts እንዲያቅዱ፣ ውሳኔ እንዲወስኑ እና መፍትሔ እንዲፈልጉ ጊዜ እና ቦታ በመስጠት መሪ እንዲሆኑ ያደርጋሉ

## በጋራ መምራት፡ የእርሶ አጋር ከሆነ መሪ ጋር አብሮ መስራት

እያንዳንዱ ቡድን፣ ዝምድና የሌላቸው፣ ምዝገባ ያጠናቀቁ፣ የኋላ ታሪካቸው የተረጋገጠ እና የሰለጠኑ ቢያንስ ሁለት የቡድን መሪዎች ሊኖሩት ይገባል። በ Girl Scouts ውስጥ ሁሉም መሪዎች እኩል ናቸው —‘ዋና’ ወይም ‘ረዳት’ የሚባሉ መሪዎች የሉም።

ከአጋር መሪዎች ጋር ያለዎት ትብብር እንደ ቡድን ለሚኖርዎት ስኬት አስፈላጊ ነው! የእርስዎ አጋር የሆነውን መሪ አስቀድመው የማያውቁት ከሆነ፣ ለትውውቅ የሚሆን ትንሽ ጊዜ በመስጠት ለቡድኑ ያለዎትን እቅድ እና ግቦች ይወያዩ። የቡድን መሪዎች በስብሰባ ወቅት ውሳኔዎችን ከአሳዳጊዎች ጋር መጋራት ይችሉ ዘንድ ከመጀመሪያው የአሳዳጊዎች ስብሰባ በፊት  ቡድኑን የሚመለከቱ አንዳንድ ውሳኔዎችን ማድረግ ይኖርባቸዋል። እነዚህም የሚከተሉትን ያካትታሉ:



- የስብሰባ ስርዓቶች፡ ቡድኑ መቼ፣ የት፣ ምን ያህል ጊዜ እና ለምን ያህል ጊዜ ይገናኛል?
- ቡድኑ ከአሳዳጊዎች ምን አይነት እርዳታ ያስፈልገዋል?
- እርስ በርሳችሁ ምን ዓይነት ግንኙነት ትጠቀማላችሁ?
- ከቡድን ቤተሰቦች ጋር ምን ዓይነት የግንኙነት መንገድ ይጠቀማሉ?
- ከሁለት አንዳችሁ በተለይም የምትፈልጓቸው፣ ወይም የማትፈልጉዋቸው ክፍሎች አሏችሁ? አንዳንድ የጋራ መሪዎች ስራዎችን እኩል ይከፋፈላሉ፣ ሌሎች ደግሞ ፕሮግራሙን የማቀድ ኃላፊነት ያለው አንድ መሪ ሲኖራቸው ሌላኛው ደግሞ አስተዳደራዊ ተግባራትን ይሰራል፡፡
- የቡድን የገንዘብ አያያዝ፡ የትኛው የቡድን መሪ ነው የቡድኑ የባንክ ሂሳብ ላይ የመፈረም ስልጣን የሚኖረው? ከጅምሩ የቡድን መዋጮ እንሰበስባለን?
- የአሳዳጊዎች የስብሰባ አጀንዳውን ያጠናቅቁ፡፡

## ሁለተኛ ሳምንት

## ስብሰባ፡ ከአገልግሎት ክፍል የእንግዳ አቀባበል ልዩ ባለሙያ ጋር የአቀባበል ክፍለ-ጊዜ ላይ መገኘት

ዝግጅቱ ሲኖር ያሳውቁዎታል! ይህ ስብሰባ ከአከባቢዎ የአገልግሎት ክፍል ጋር በማስተዋወቅ ያግዝዎታል- ድጋፍ የሚሰጥዎ የአካባቢዎ የበጎ ፈቃደኞች ቡድን የትስስር መረብ፡፡ አንድ ሰው ጥያቄዎችን እንዲጠይቅ ከማድረግ የተሻለ ድጋፍ እንደሌለ እናውቃለን፣ ስለዚህ ያንን ግንኙነት ለመፍጠር ከእንግዳ አቀባበል ባለሙያው ጋር መገናኘቱ አስፈላጊ ነው!

የተለመዱ አንዳንድ አጀንዳዎች፡

- የአገልግሎት ክፍል ቡድን የበጎ ፈቃደኞች የመገኛ መረጃ
- የበጎ ፈቃደኞች መሰረታዊ መመሪያዎች የወረቀት ቅጂ
- የአሳዳጊዎች ስብሰባ፡ ጥያቄዎችን የመጠየቂያ ወይም አጀንዳ ላይ አስተያየት የመቀበያ ጊዜ
- የ gsLearn ማጣሪያ፡ ትምህርቶች እንዴት እየሄዱ ነው?

## ስብሰባ፡ በመጀመሪያው የአገልግሎት ክፍል ስብሰባ ላይ መገኘት

ቡድኖች እያንዳንዱ የአገልግሎት ክፍል ስብሰባ ላይ ተወካይ መላክ አለባቸው።

## የአገልግሎት ክፍል ቡድን በጎ ፈቃደኞች እገዛ ለመስጠት ዝግጁ ናቸው!

እያንዳንዱ ቡድን፣ በሚገናኝበት ቦታ ላይ የተመሰረተ የአገልግሎት ክፍል አለው። ችግሮችን የሚፈቱ እና ቡድኖች በበጎ ፈቃደኞች መሰረታዊ መመሪያዎች መሰረት መስራታቸውን የሚያረጋግጡ የአካባቢው በጎ ፈቃደኞች የአገልግሎት ክፍሎችን ያስተዳድራሉ። እርስዎን የሚረዱ እና የሚመድቡ የአገልግሎት ክፍል ቡድን በጎ ፈቃደኞች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡

የአገልግሎት ክፍል አስተዳዳሪዎች፡ Hold የአካባቢውን ወርሃዊ የድጋፍ፣ የስልጠና እና የፕሮግራም ስብሰባዎችን ያካሂዳሉ - ቡድኑ ተወካይ መላክ አለበት። እንደ አስፈላጊነቱ አለመስማማቶችን ይፈታል።

የአገልግሎት ክፍል የምዝገባ ኃላፊ፡ ወጣቶችን እና አዋቂዎችን በምዝገባ እና በኋላ ታሪክ የማረጋገጥ ሂደት ወቅት ያግዛል።

የአገልግሎት ክፍል ገንዘብ አስተዳዳሪ፡ የቡድን ገንዘብ አስተዳዳሪን ያሰለጥናል (የቡድን መሪ መሆን አይችልም)፣ ከቡድኑ ወርሃዊ የባንክ መግለጫዎችን ይሰበስባል እንዲሁም ትክክለኛ የገንዘብ መመሪያዎች ጥቅም ላይ መዋላቸውን ይከታተላል።

የአገልግሎት ክፍል የእንግዳ አቀባበል ባለሙያ፡ ሁሉንም የቡድን በጎ ፈቃደኞች በመቀበል ከስልጠና እና የአገልግሎት ክፍል ድጋፍ ጋር ያገናኛቸዋል።

የአገልግሎት ክፍል ቡድን አደራጆች፡ ከትምህርት ቤት፣ ከመንፈሳዊ አምልኮ ቤት ወይም ከማህበረሰብ ማእከል ጋር ግንኙነት ያላቸው። ቡድኖች ምስረታ እና ማቋቋም ላይ ይረዳል፤ አዲስ አባላትን ነባር ቡድኖች ውስጥ ይመድባል፤ ቤተሰቦች እንዲቀላቀሉ ያነሳሳል!

ወጣት አባላት ማንኛውንም ቡድን መቀላቀል ይችላሉ - በትምህርት ቤታቸው ወይም በመንፈሳዊ አምልኮ ቤታቸው ውስጥ ብቻ አይደለም!

ከአገልግሎት ክፍልዎ እስካሁን መልዕክት አልደረስዎትም?

ለመገናኘት membershipsupport@gscnc.org ላይ ያነጋግሩ!

# ሁለተኛ ሳምንት

## የ gsLearn ትምህርት፡ የተንከባካቢ ተሳትፎ

## እያንዳንዱ ቤተሰብ በበጎ ፈቃደኝነት ያገለግላል!



የመጀመሪያውን የቡድን ስብሰባ ከማድረግዎ በፊት በዓመቱ ውስጥ የሚያስፈልጉዎትን ድጋፍ እና ግብዓቶች ግምት ውስጥ ያስገቡ። መረጃ ለመስጠት እና ቤተሰቦች በቡድን ውስጥ የበጎ ፈቃደኝነት ሚና እንዲጫወቱ እንዲሁም ተጨማሪ የወላጅ በጎ ፈቃደኞችን ለማሰባሰብ የወላጅ ስብሰባዎችን በዓመት ሁለት ጊዜ ያካሂዱ። ማንም ላይ ጫና የማይፈጥር ስኬታማ ቡድን ለመፍጠር ዘጠኝ የበጎ ፈቃድ ሚናዎችን ዘጠኝ የተለያዩ ሰዎች መያዝ አለባቸው፡

- 2 የቡድን መሪዎች (ሁልጊዜም አንዷ ሴት ሆና ሁለት የማይዛመዱ አዋቂዎች መሆን አለባቸው - ማንኛውም አዋቂ በማንኛውም ጊዜ ከልጅ ጋር ብቻውን ሊሆን አይችልም)
- የቡድን የCookie አስተዳዳሪ የቡድን ገንዘብ አስተዳዳሪ
- የቡድን የ Fall Product አስተባባሪ የቡድን የ SHARE አስተባባሪ
- ከቤት ውጪ ቆይታ/ከቤት ውጪ የምግብ ዝግጅት ባለሙያ አዋቂ የመጀመሪያ ደረጃ የህክምና እርዳታ ሰጪ
- ሹፌር/አጃቢ - የመስክ ጉዞዎችን ያቅዳል፣ ያጅባል እንዲሁም የወላጅ ግንኙነት/ፈቃድን ያስፈጽማል

**እነዚህ ሚናዎች እንደ የ GSUSA አዋቂ አባል መመዝገብን እና የኋላ ታሪክ ማጣሪያ ማጠናቀቅን ይጠይቃሉ።**

**አሁን ላይ እየሰሩ ያሉ የቡድን በጎ ፈቃደኞች፣ ለተወሰነ ሚና እንዲመዘገቡ ለአዲስ በጎ ፈቃደኞች የገጽ አገናኝ መላክ ይችላሉ፡**

1. ወደ My GS Sign In/My Account መግባት
2. My Troops (የእኔ ቡድን) የሚለውን ይጫኑ
3. ከዝርዝሩ ውስጥ የሚገኘውን ሚና ይጫኑ
4. የገጽ አገናኙን ለመቅዳት የማጋሪያ ምልክቱን ጠቅ ያድርጉ
5. ለአዲስ በጎ ፈቃደኛ ለመላክ አገናኙን የኢሜይል መልዕክት ላይ ይለጥፉ!

**"ጓደኞች እና የቤተሰብ በጎ ፈቃደኞች" የኋላ ታሪክ ማጣሪያን የማይጠይቅ ሲሆን** እንደ "የመክሰስ ወላጅ" ወይም በአገልግሎት ክፍል ስብሰባዎች ላይ የቡድን ተወካይነት ሚናዎች ውስጥ ለሚያገለግሉ በጎ ፈቃደኞች ነው።

**ጓደኞች እና የቤተሰብ በጎ ፈቃደኞች**

በተለያዩ ምክንያቶች የኋላ ታሪክ ማጣሪያን ለማጠናቀቅ የማይችሉ ወይም የማይፈልጉ አዋቂዎች በቡድንዎ ውስጥ ሊኖሩዎት ይችላሉ። እያንዳንዱ ቤተሰብ በበጎ ፈቃደኝነት እንዲሰራ አጥብቀን የምናበረታታ ቢሆንም፣ አንድን አዋቂ አባል ልጁ እንድትሳተፍ የኋላ ታሪክ ማጣሪያን የሚጠይቅ ሚና እንዲይዝ መጠየቁ ተገቢ አይደለም። አንድ አዋቂ የኋላ ታሪክ ማጣሪያን የሚጠይቅ ሚና መያዝ ካልቻለ፣ ቡድኑን ሊደግፍበት የሚችልባቸው አንዳንድ የጓደኞች እና የቤተሰብ የበጎ ፈቃድ እድሎችን ያግኙ።

## ተግባር፡ ለአሳዳጊዎች ስብሰባ መርሐግብር ማስያዝ

## ተግባር፡ ቤተሰቦችን ለማግኘት እና የአሳዳጊዎች ስብሰባ ላይ እንዲገኙ ለመጋበዝ የቡድኑን ዝርዝር መግለጫ ይጠቀሙ

### የአሳዳጊዎች ስብሰባዎች፡ ማህበረሰብ እና ግንኙነት

ይህን ብቻዬን እንደማላረገው ቃል እገባለሁ!
ወላጆች፣ ጓደኞች እና ሌሎች የቤተሰብ አባላት ጊዜን፣ ተሞክሮን እና ሀሳቦችን ለአዲስ ቡድን መስጠት ይችላሉ፣ ስለዚህም ከመጀመሪያው ጀምሮ እንዲሳተፉ ያድርጉ። ሁሉም ቤተሰቦች በተወሰነ አቅም በበጎ ፈቃደኝነት ያገለግላሉ።

የአሳዳጊዎችን ስብሰባ ሲያዘጋጁ የሚከተሉት እድሎች እንደሚገኙበት አጋጣሚ ያስቡት፡
ከ Girl Scouts እና ከቤተሰቦቻቸው ጋር የሚተዋወቁበት
የቡድን ተግባራት ላይ በበጎ ፈቃደኝነት ለማገዝ እንዲመዘገቡ እያንዳንዱን ቤተሰብ የሚጠይቁበት
በሴት ልጆች የሚመሩ እንቅስቃሴዎች እና በጀት አወጣጥ፣ የስብሰባ/የእንቅስቃሴ መርሃ ግብር፣ የአሳዳጊ ተሳትፎ፣ የመገናኛ ዘዴ፣ ወዘተ ጨምሮለ ቡድኑ ግልፅ መመሪያዎችን የሚያስቀምጡበት።

የስብሰባ ዝግጅት ማረጋገጫ ዝርዝር፡

- የስብሰባ ጊዜ እና እንደ ቤትዎ፣ የአከባቢው ትምህርት ቤት፣ ቤተ ክርስቲያን ወይም ቤተ-መጽሐፍት መሰል የስብሰባ ቦታ ያዘጋጁ።
- ሁሉንም ወላጆች እና ወጣቶች ለመጋበዝ Volunteer Toolkit (በበጎ ፈቃደኞች የመገልገያ ስብስብ) ውስጥ የሚገኘውን የቡድን ዝርዝር መግለጫ ይጠቀሙ።
- የጤና መዝገብ ቅጽ እና Meeting My Girl Scout ቅጽ (www.gscnc.org – መፈለጊያው ውስጥ ቅጾችን ይፃፉ) በቡድኑ ውስጥ ለተመዘገበ እያንዳንዱ ቤተሰብ ይላኩ። (የተጠናቀቁ ቅጂዎች የቡድኑ መሪ ጋር በመዝገብ ይቆያሉ)
- በጎ ፈቃደኞች እነማን እንደሆኑ ለመመዝገብ ለእያንዳንዱ የበጎ ፈቃደኞች ሚና የምዝገባ ወረቀት ይኑርዎት። (ለማብራሪያዎች የበጎ ፈቃደኞች መሰረታዊ መመሪያዎችን ይመልከቱ።)
- ከወላጆች ጋር በሚነጋገሩበት ወቅት ልጆች የሚያጠናቅቁት እንቅስቃሴ ወይም እደ-ጥበብ ያቅዱ።
- መናገር እና ማጋራት የሚፈልጉትን መረጃ ይለማመዱ።
- ያስታውሱ - ይህ ከ Girl Scouts ጋር የመጀመሪያቸው ተሞክሮ ሊሆን ይችላል! Girl Scouts ዙሪያቸው ባለው አለም ውስጥ አዳዲስ ነገር ለማግኘት፣ ግንኙነት ለመፍጠር እና እርምጃ ለመውሰድ በሚያደርጉት ጉዞ ሲያግዟቸው እርስዎም ጥሩ ጊዜ እያሳለፉ መሆንዎን ያረጋግጡ።.



## ሦስተኛ ሳምንት

# ስብሰባ፡ የአሳዳጊዎች ስብሰባን ማዘጋጀት

**ተግባር፡ የ Girl Scout የጤና መዝገብ ቅጾችን እና Meet My Girl Scout ቅጾችን ይሰብስቡ**

**ተግባር፡ ለቡድን ኮሚቴ የሚያገለግሉ በጎ ፈቃደኞችን ይለዩ**

### የአሳዳጊዎች ስብሰባ አጀንዳ ምሳሌ

- እንኳን ደህና መጣችሁ እና መግቢያዎች፡ አሳዳጊዎችን እርስ በእርስ ያስተዋውቁ እና ስለ Girl Scouts አጠቃላይ እይታ ገለጻ ይስጡ። እነሱንም ለመተዋወቅ ስለ እያንዳንዱ Girl Scout ጥያቄዎችን ይጠይቁ!
- የቤተሰብ ተሳትፎ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ያካፍሉ እንዲሁም ለተወሰኑ የበጎ ፈቃደኛ ሚናዎች ድጋፍ ይጠይቁ።
- የስብሰባ ቦታ፣ ቀን እና ሰዓት፣ የደንብ ልብስ እና የቡድን መዋጮን በሚመለከት ተወያዩ።
- በቡድን መሪዎች እና በአሳዳጊዎች መካከል የሚጠበቁ የግንኙነት እና የምላሽ ጊዜዎችን ያስቅምጡ። መልዕክቶችን የማንበብ እና ምላሽ የመስጠት አስፈላጊነት ላይ አፅንዖት ይስጡ።
- አሳዳጊዎች የጤና መዝገብ እና የ Meet my Girl Scout ቅጾችን አሟልተው እንዲያስገቡ ያድርጉ (ድንገት ወላጆች ቅጂ ሳይዙ ሊመጡ ስለሚችሉ ተጨማሪ ባዶ ቅጂዎችን ይዘው ይምጡ)።
- ቡድኑ በዚህ አመት የሚሳተፍባቸውን የእንቅስቃሴ ዓይነቶች ይወያዩ።
- ከአሳዳጊዎች ለሚነሱ ማናቸውም ጥያቄዎች መልስ ይስጡ፣ እንዲሁም በስብሰባው ወቅት ሊመልሷቸው የማይችሏቸውን ማናቸውም ጥያቄዎች በኋላ ተከታትለው እገዛ ለማድረግ አስታውሰው ይያዙ።



**የተሟላ፣ ሊስተካከል የሚችል የአሳዳጊዎች ስብሰባ አጀንዳ፣ በ GSCNC፣ New Leader Rally ላይ ማግኘት ይችላሉ።*

የ Girl Scout የጤና መዝገብ ቅፆች እና Meet My Girl Scout ቅፆች፣ ቡድንዎ ጥሩ ጅምር እንዲኖረው ያግዛሉ! ወደ gscnc.org በመሄድ እና 'አባላት' > 'ቅጾች እና ሰነዶች' የሚለውን ጠቅ በማድረግ ያግኟቸው።

**ሦስተኛ ሳምንት**

## የ gsLearn ትምህርት፡ የቡድን መሪ መመሪያዎች

1. የ Girl Scout ቃል ኪዳን + ህግን ከቡድንዎ ጋር እንዴት እንደሚለማመዱ (10 ደቂቃ)
2. በቡድንዎ ውስጥ ያሉ Girl Scouts እንዴት መተዋወቅ እንደሚችሉ (5 ደቂቃዎች)
3. የቡድን ስብሰባ እንዴት ማቀድ እንደሚቻል (5 ደቂቃዎች)
4. የደህንነት መስፈርቶችን እንዴት ማስተዳደር እንደሚቻል (15 ደቂቃዎች)
5. በወጣት የሚመራ በጀት እንዴት መቆጣጠር እንደሚቻል (10 ደቂቃ)
6. ግጭትን እንዴት መቆጣጠር እንደሚቻል (10 ደቂቃዎች)
7. ወደ ቡድንዎ የሚቀላቀሉ አዳዲስ Girl Scouts እንዴት እንደሚቀበሉ (5 ደቂቃዎች)



## የምክር ቤት ሰራተኞች፡ ከሰራተኛ አባልነት ባለሙያ ጋር ይገናኙ (ይደውልሎታል!)

የ Nation's Capital Girl Scout ምክር ቤታችን (GSCNC) ክልላችን ውስጥ ባሉ ወጣቶች እና አዋቂ አባላት (በጎ ፈቃደኞች እና ሰራተኞች) የተዋቀረ ነው። የአገልግሎት ክፍሎች እና ማኅበራት are ]በአንድ የተወሰነ ክልል ውስጥ የቡድኖችን ስራ የሚደግፉ በጎ ፈቃደኞችን ያቀፉ ናቸው። እነዚህ በጎ ፈቃደኞች የቡድን በጎ ፈቃደኞችን ይመድባሉ፣ ያሰለጥናሉ እንዲሁም በቀጥታ ድጋፍ ይሰጣሉ።

በእነዚህ አካባቢዎች ያሉ ወጣቶች እና በጎ ፈቃደኞች በአባልነት አካባቢው ሰራተኞች ይደገፋሉ። የአባልነት ባለሙያዎች እና አስተባባሪዎች የአገልግሎት ክፍሎችን እና ማህበራትን በቀጥታ እንዲረዱ የተመደቡ ናቸው።

በተጨማሪም ሌሎች በርካታ ዲፓርትመንቶች በክልላችን ውስጥ ያለውን የ Girl Scout እንቅስቃሴን ይደግፋሉ። የአዋቂ በጎ ፈቃደኞች እድገት (AVD) ስልጠና እና የአዋቂዎችን እውቅና ይደግፋል። የፕሮግራሙ ዲፓርትመንት ከፍተኛ ሽልማቶችን እና የማህበረሰብ ፕሮግራም አጋሮችን

ከአባልነት ባለሙያዎ እስካሁን መልዕክት አልደረሰዎትም?
ለመገናኘት **membershipsupport@gscnc.org** ላይ ያነጋግሩ!

ይደግፋል። የምርት ፕሮግራም የ Fall Sale እና የ Cookie ፕሮግራምን ይደግፋል፣ የካምፕ አገልግሎት፣ ከቤት ውጪ ቆይታ ፕሮግራማችንን ይደግፋል እንዲሁም የግብይት/ግንኙነት የ Girl Scout እንቅስቃሴያችን በህዝብ ዘንድ የሚታይ መሆኑን ያረጋግጣል። እነዚህ እርስዎን እና ልጆቻችንን ከሚደግፉት ከ120 በላይ ሰራተኞች ውስጥ ጥቂቶቹ ናቸው።

የዩኤስኤ Girl Scouts (GSUSA) በመላው ዩኤስ ከ100 በላይ ምክር ቤቶችን ስራ ከ110 ዓመታት በላይ እየደገፈ ያለ የ Girl Scout እንቅስቃሴ ብሔራዊ ድርጅት ነው። ዋና መስሪያ ቤቱ በኒውዮርክ ከተማ፣ ኒው ዮርክ ነው። የGirl Scout አባልነት ክፍያ 100% GSUSAን ይደግፋል።

## አራተኛ ሳምንት

# የ gsLearn ትምህርት፡ የቡድን ገንዘብ አስተዳደር እና አማራጭ መመሪያዎች

የቡድን ገንዘብ አስተዳደር በየአመቱ በቡድን ገንዘብ አስተዳዳሪ እና በሁሉም **የቡድን መሪዎች** ይወሰዳል። የቡድን መሪዎች ይህንን ሚና የሚይዘውን የቡድን ኮሚቴ አባል መደገፍ እንዲችሉ የቡድን ገንዘብ አስተዳዳር ስልጠናን መውሰድ አለባቸው። የቡድን በጀት እንዴት እንደሚወጣ ይማሩና በሁሉም የፕሮግራም ደረጃዎች ላይ ያሉ አባላትን እድሜን በሚመጥን መንገድ የቡድኑ የገንዘብ ውሳኔዎች ላይ ያሳትፏቸው።

የዚህ ሳምንት አማራጭ መመሪያዎች፡

1. የበጎ ፈቃደኞች መገልገያ ስብስብን እንዴት መጠቀም እንደሚቻል (10 ደቂቃዎች)
2. የ Girl Scout ሽልማቶችን እንዴት ማግኘት እንደሚቻል - የእውቅና አርማዎች፣ ጉዞዎች፣ ተለጣፊ ምልክቶች (5 ደቂቃዎች)
3. የ Girl Scout የደንብ ልብስ ምንድን ነው (5 ደቂቃ)
4. ከመደበኛው የስብሰባ ሰዓት እና ቦታ ውጭ የመስክ ጉዞን ወይም እንቅስቃሴን እንዴት ማቀድ እንደሚቻል (15 ደቂቃ)
5. ቡድኔን የማሳድገው እንዴት ነው (5 ደቂቃ)
6. Rallyhoodን እንዴት መጠቀም እንደሚቻል (5 ደቂቃዎች)
7. ቀጣይ እርምጃዎች

# ተግባር፡ የቡድን ገንዘብ አስተዳዳሪን ከአገልግሎት ክፍል ገንዘብ አስተዳዳሪ ጋር ማገናኘት

የአገልግሎት ክፍል ገንዘብ አስተዳዳሪዎ የእርስዎን ቡድን ይረዳል፡

- የቡድን ገንዘብ አስተዳዳሪዎች ከ gsLearn የቡድን ገንዘብ አስተዳደር ስልጠና ጋር እንዲገናኙ ያግዛል።
- ለባንክ ፈቃድ ደብዳቤ ጥያቄ ያቀርባል፣ የቡድኑ የባንክ ሒሳብ ሶስተኛ ደረጃ ባለቤት ነው እንዲሁም በአገልግሎት ክፍሉ ተመራጭ ባንክ ውስጥ የቡድን የባንክ ሂሳብ በማቋቋም ይረዳል።
- አዲስ የቡድን ሂሳብ በመክፈት እና በመዝጋት ይረዳል።
- ሁሉንም ቡድኖች በተገቢው ሂደቶች በማስተማር ያግዛል።
- የቡድኑን ሁሉንም የባንክ መግለጫዎች እና ደረሰኞች ይሰበስባል እንዲሁም የባንክ ደብተር መዛባቶችን ይመረምራል።
- የአገልግሎት ክፍል ባንክ እና አመታዊ በጀት ገንዘብ አስተዳዳሪ

ከሁለቱ የቡድን መሪዎች አንዱ በቡድን ባንክ ሂሳብ ላይ ፈራሚ መሆን አለበት። እርስዎ እና የስራ ባልደረባዎ ማን እንደሚሆን ተወያይታችሁ መወሰናችሁን ያረጋግጡ!

# ተግባር፡ ለመጀመሪያው የቡድን ስብሰባ መርሐግብር ማውጣት

የትኛውም የቡድን አመት ከሌላ ቡድን አመት ጋር አይመሳሰልም ነገር ግን የ Girl Scout ቡድኖች፡

- Girl Scouts ጠንካራ ግንኙነት እንዲፈጥሩ ለማገዝ በመደበኛነት ይገናኛሉ (ቢያንስ በወር ሁለት ጊዜ)።
- እንደ ከቤት ውጪ መውጣት፣ የመስክ ጉዞ ማድረግ፣ በ Girl Scout ዝግጅቶች ላይ መሳተፍ፣ የማህበረሰብ አገልግሎትን ማጠናቀቅ ወይም ገንዘብ የማግኛ ግቦችን ማስቀመጥ እና በምርት ፕሮግራሞች ላይ መሳተፍ ያሉ የተለያዩ ዓላማ ያላቸው እንቅስቃሴዎችን ያደርጋሉ።
- እንደ ስነ-ስርዓቶች ወይም መዝሙሮች ባሉ የ Girl Scout ወጎች ላይ ይሳተፋሉ።

## የዴይዚ Girl Scout ቡድኖች

በሂደቱ ለማገዝ ለአዲስ ዴይዚ Girl Scout የተዘጋጀውን Girl Scout Experience Box በመጠቀም የስብሰባ/የተግባራት መርሃ ግብር ይወስናሉ።

## ብራውኒ፣ ጁኒየር፣ ካዴት፣ ሲኒየር እና አምባሳደር ቡድኖች

ዕቅዶችን፣ የመመሪያ ጽሑፎችን፣ የቁሳቁስ ዝርዝሮችን፣ የእውቅና አርማ እና የጉዞ መስፈርቶችን እና ሌሎችንም ለማግኘት ወደ Volunteer Toolkit (የበጎ ፈቃደኞች መገልገያ ስብስብ) ይሂዱ! ለተጨማሪ ሀሳቦች፣ መርጃዎች እና የደረጃ-በደረጃ ዕቅዶች፣ በ gsLearn እና በእርስዎ የፕሮግራም ደረጃ ስልጠና ላይ "የበጎ ፈቃደኞች መገልገያ ስብስብን እንዴት እንደሚጠቀሙ" የሚለውን ይመልከቱ!

## ታላቅ የቡድን ስብሰባ ያቅዱ እና ይምሩ

**የ Girl Scout ስብሰባዎች ደህንነታቸው የተጠበቀ እና አዝናኝ ናቸው! በበጎ ፈቃደኞች የ<u>ምንደገፍ</u> በሴት ልጆች የ<u>ምንመራ</u> ድርጅት ነን።**

**ጅማሬ** - Girl Scouts በቦታው ደርሰው ስብሰባው እስኪጀመር ድረስ በተግባር ላይ እንዲቆዩ ለማድረግ የሚያሳትፍ እንቅስቃሴ ያቅዱ። ምሳሌዎች፡ ቀለም መቀባት፣ የግል ማስታወሻ መጻፍ ወይም የስም መለያ ባጅ መስራት። (5 ደቂቃዎች)።

**መክፈቻ** - Girl Scouts የስብሰባ መክፈቻቸውን ይወስኑና ይመራሉ - አብዛኛዎቹ የሚጀምሩት በGirl Scout ቃል ኪዳን እና ህግ፣ ቀላል የሰንደቅ አላማ ስነ-ስርዓት እና መዝሙር ነው። (5-10 ደቂቃዎች)፡፡

**ንግድ** - ይህ ጊዜ የ Girl Scout የደህንነት መመሪያዎችን፣ የቡድኑን በጀት እና ገንዘብ የማግኘት ግቦች፣ ማድረግ የሚፈልጓቸውን የመስክ ጉዞዎች፣ የትኞቹን የእውቅና አርማዎች ወይም ተለጣፊ ምልክቶች ማግኘት እንዳለባቸው ጨምሮ መጪ ስብሰባዎቻቸውን እንዲያቅዱ እንዲሁም መዋጮ እንዲሰበስቡ እና ማሳወቂያዎችን እንዲናገሩ የሚፈቅዱበት ጊዜ ነው (10-15 ደቂቃዎች)።

**ተግባራት** - ቡድንዎ የእውቅና አርማ እና ጉዞዎችን ለማግኘት የሚያስችሏቸውን አስቀድመው የተመረጡት ተግባራት በሚያጠናቅቁበት ጊዜ ይደግፏቸው። ይህ የስብሰባ ክፍል በቡድን መሪዎች እና በበጎ ፈቃደኞች እየተደገፈ በዋነኝነት በሴት ልጅ የሚመራ መሆን አለበት። (30-45 ደቂቃዎች)

**ጽዳት** - Girl Scouts ሁልጊዜ አንድን ቦታ ሲያገኙት ከነበረው በላይ ንጹህ አድርገው ይሄዳሉ! (5 ደቂቃዎች)

**መዝጊያ** - ልክ እንደ መክፈቻው፣ እያንዳንዱ ቡድን መዝጊያው እንዴት እንደሚሆን መወሰን ይችላል፣ ለምሳሌ እጅ ለእጅ በመያያዝ የጓደኝነት ክብ ሰርቶ መዘመር፡፡ ስለ መጪ ስብሰባዎች እና ዝግጅቶች ማናቸውንም አስፈላጊ አዳዲስ መረጃዎች ወይም አስታዋሾች ለአሳዳጊዎች ያቅርቡ።

በእያንዳንዱ ስብሰባ መጨረሻ ላይ ከ"ንግድ" ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ለመፍታት 5 ደቂቃ የሚወስድ የወላጅ/አሳዳጊ አጭር ውይይት እንዲኖር ለማድረግ ያስቡበት።

የመሰብሰቢያ ቦታ እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ እርግጠኛ አይደሉም? ሀሳቦችን ለማግኘት **ከቡድኑ አደራጅ** ወይም ቡድኑን ለመመስረት ከረዳዎት **የአባልነት ባለሙያ** ።

# ስድስተኛ ሳምንት

## ተግባር፡ የመጀመሪያውን የቡድን ስብሰባ ማድረግ

### የመጀመሪያው ስብሰባዎ ላይ ያልተገኙ ሰዎች ነበሩ?

የ Girl Scouts ቡድን አባልነትን በሚመለከት መጀመሪያ የመጣ፣ መጀመሪያ የሚስተናገድ መሆኑን እና ቦታዎችን ለሰው ማስቀመጥ እንደማንችል ወይም ለክፍት ቦታዎች ተጠባባቂ ዝርዝር ሊኖረን እንደማይችል ማስታወስ አስፈላጊ ነው። አንድ ልጅ የሚመዘገብበት ክፍት ቦታ እንደተገኘ፣ ብቁ በሆነ ክፍል ውስጥ ያለ ማንኛውም ሰው መመዝገብ እና ወደ ቡድኑ መቀላቀል ይችላል!

የማይገኙ ልጆች አሳዳጊዎችን ያነጋግሩ። አንድ አሳዳጊ ተለዋጭ ምደባ ለማግኘት እርዳታ የሚያስፈልገው ከሆነ የቡድኑን አደራጅ ወይም የአባልነት ባለሙያውን ያሳውቁ።

## ተግባር፡ ለአዲስ መሪ የተዘጋጁ ትምህርታዊ ጉባኤዎችን ኦንላይን ላይ መመልከት

Girl Scouts Nation's Capital፣ አዳዲስ መሪዎቻችንን ለመደገፍ ሲል ለአዲስ መሪ የተዘጋጁ ትምህርታዊ ጉባኤዎችን በወር አንድ ጊዜ፣ በወሩ የመጨረሻው ረቡዕ ያቀርባል። ሁሉም ስብሰባዎች Zoom ላይ ይካሄዳሉ። እያንዳንዱ ስብሰባ ለመጀመሪያዎቹ 30 ደቂቃዎች የተለየ ርዕስ የሚኖረው ሲሆን ከዚያ ተጨማሪ ድጋፍ ለመስጠት መድረኩ ለጥያቄ እና መልስ ክፍት ይሆናል፡፡

ሁሉንም ትምህርታዊ ጉባኤዎች እና የምዝገባ ገጽ አገናኞች እዚህ በ New Leader Rally ላይ ማግኘት ይችላሉ (ገጽ 8 ይመልከቱ)።

## ተግባር፡ የቡድን የመረጃ ማህደርን ማጠናቀቅ

ቡድንዎ በመስመር ላይ በሚገኘው የቡድን ማህደራችን ውስጥ ትክክለኛ መረጃ እንዳለው ማረጋገጥ ከአንድ ቡድን መሪ ቁልፍ ኃላፊነቶች ውስጥ አንዱ ነው! የቡድንዎን ወቅታዊ ዝርዝር ለማግኘት የአገልግሎት ክፍልዎን የምዝገባ ኃላፊ ይጠይቁ። የመጀመሪያ ስብሰባዎን አድርገው የጨረሱ በመሆኑ፣ መረጃ የማዘመኛ ጊዜው አሁን ነው። ይህንን ለማድረግ ቀጣዩን ገጽ አገናኝ ይጎብኙ፡

https://gscnc.jotform.com/membership/troop-catalog-update

## የ gsLearn ትምህርት፡ በፕሮግራም ደረጃ የሚያስፈልጉ መሰረታዊ ነገሮች

ይህ ኮርስ ለአንድ የተወሰነ የፕሮግራም ደረጃ የGirl Scout መሆን ምን ማለት እንደሆነ፣ የ Girl Scout አመራር ተሞክሮ፣ የእውቅና አርማዎች እና ጉዞዎች እንዲሁም የደህንነት መሰረታዊ ነገሮች፣ በ Girl Scout አመት ውስጥ የሚገኙ መርጃዎች እና የእድገት ሂደቶችን ያስተዋውቀዎታል።



## ስምንተኛ ሳምንት

## ተግባር: የቡድን ገንዘብ አስተዳዳሪው የባንክ ሂሳብ በሚከፍቱበት ወቅት እገዛ ያድርጉላቸው

የአገልግሎት ክፍል ገንዘብ አስተዳዳሪዎ በዚህ ተግባር ሂደት ውስጥ ይመራዎታል። ከእርስዎ የአገልግሎት ክፍል ገንዘብ አስተዳዳሪ ጋር የመገናኘት ችግር ካጋጠመዎት፣ እባክዎን ለእርዳታ membershipsupport@gscnc.org ላይ ያናግሩ!

## የ gsLearn ትምህርት: ለቀጥታ ስርጭት ክፍለ-ጊዜዎ ይመዝገቡ

## የ gsLearn ትምህርት: DEIA ላይ ቁርጠኝነት እና አካታች ቋንቋ

## ሶስተኛ ወር

## የ gsLearn ትምህርት: በቀጥታ ስርጭት ክፍለ-ጊዜ ላይ ይገኙ!

# አሳክተውታል!

የቡድን መሪነት የመጀመሪያዎቹን ሶስት ወራት በማጠናቀቅዎ እንኳን ደስ አለዎት! ባለፉት ሶስት ወራት ውስጥ፣ አጋርዎ ከሆነ መሪ ጋር እንዴት መስራት እንደሚችሉ አውቀዋል፣ ቤተሰቦች በ Girl Scout ተሞክሯቸው ውስጥ እንዲሳተፉ አግዘዋል፣ ስለ Girl Scouting እና ስለ እርስዎ አገልግሎት ክፍል ብዙ ተምረዋል፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ የእርስዎ Girl Scouts ለህይወት ዘመን የሚቆይ ተልዕኮቻቸውን በሚጀምሩበት ወቅት ማግኘት ጀምረዋል።


አሁንም በድጋሚ፣ ለልጆቻችን ይህን ወሳኝ ሚና ስለተጫወቱ እናመሰግናለን! የተሻለ ነገን ለመገንባት እየረዱ ሲሆን አስተዋጽዖ በማበርከትዎት በጣም ደስ ብሎናል።

# ማለም፣ ሰርቶ ማግኘት፣ ማድረግ

ሁሉም Girl Scouts የገንዘብ ቼክ ከማጻፍ ይልቅ ለ Girl Scout የሚውለውን ገንዘብ ሰርተው እንዲያገኙ ይበረታታሉ። ለምን? ለዚያ አስደናቂ የመስክ ጉዞ የዋለውን ገንዘብ ሰርታ እንዳገኘች የምታውቅ አንዲት የአፀደ ህፃናት ተማሪን ወይም ሰርታ ባገኘችው ገንዘብ ወደ ስዊዘርላንድ እየተጓዘች ያለች አንዲት የ11ኛ ክፍል ተማሪን ያስቧት:: የሥራ ፈጠራ ለ Girl Scouts ህይወትን የሚቀይሩ ተሞክሮዎችን የሚፈጥር ሲሆን ሌላ ፕሮግራም ሊያደርገው በማይችለው መልኩ የገንዘብ አያያዝ እውቀትን ይገነባል።

**አልሚው፣ ሰርተሽ አግኚው፣ አድርጊው። Girl Scout የሚለየው በዚህ ነው።**

የ Girl Scout Cookie Program እና Fall Product Program፣ Girl Scouts እንዲያልሙ፣ ሰርተው እንዲያገኙ፣ እንዲያደርጉ እንዲሁም **አምስት ወሳኝ ክህሎቶችን** እንዲያዳብሩ ለመርዳት የተዘጋጁ ዕድሎች ናቸው:



**ግብ ማስቀመጥ**

የንግድ ሥራ እቅድ እንዴት ማዘጋጀት እንደሚቻል



**ውሳኔ መስጠት**

በጥልቀት ማሰብ እና ችግሮችን መፍታት



**የገንዘብ አያያዝ**

በቀጥታ የደንበኞችን ገንዘብ ማስተናገድ



**ማህበራዊ ችሎታዎች**

ከማህበረሰቡ አባላት ጋር መገናኘት እና በራስ መተማመንን ማዳበር



**የንግድ ሥነ-ምግባር**

እንደ ሀቀኝነት እና ታማኝነት ያሉ አወንታዊ እሴቶችን ማዳበር

**FALL PRODUCT** ለዓመቱ መጀመሪያ እና አጋማሽ ገንዘብ ለማግኘት ከሴፕቴምበር እስከ ኖቬምበር ባለው ጊዜ ይካሄዳል።

የ **COOKIE PROGRAM** ለዓመቱ መጨረሻ እና ለሚቀጥለው ዓመት መግቢያ ገንዘብ ለማግኘት ከዲሴምበር እስከ ማርች ድረስ ይካሄዳል።

ሁለቱም ፕሮግራሞች በአካል እና በምናብ (ቨርቹዋል) ለሚደረግ ተሳትፎ እድሎች አሏቸው!

የገቢው 100% ቡድኖችን እና Girl Scouts ን ለመደገፍ በአካባቢው ይቆያል!

የቡድን ገቢ ለቡድኑ በጋራ ጥቅም ላይ ይውላል - በተሸጠው መጠን ላይ በመመስረት ማንም ተጨማሪ ገንዘብ የማግኘት መብት የለውም።

**እንደ ቡድን መሪ በምርት ፕሮግራም ውስጥ የሚኖርዎት ሚና:**

- ብቻዎን አያድርጉት! ቡድኖች የቡድን መሪ ያልሆነ የቡድን Cookie አስተዳዳሪ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል ይህም የሚሆነው ሁለቱም ክብደት ያላቸው ስራዎች በመሆናቸው ነው::
- ገንዘብ የማግኘት የእውቅና አርማዎችን እና ግብ አቀማመጥን በቡድንዎ ፕሮግራም ውስጥ ያካትቱ (**ፍንጭ፡** እቅድ ለማውጣት እንዲረዳዎ የ Girl Scout Experience Box ስብሰባዎችዎን ወይም VTK ይጠቀሙ!)
- የአገልግሎት ክፍልዎን እርዳታ ይጠይቁ፡ በፕሮግራሙ ውስጥ የሚያሻግርዎት ልምድ ያለው የቡድን መሪ ሊያገኙ ይችላሉ፣ ወይም የእርስዎን Girl Scouts በመጀመሪያው የተሞክሮ ዘመናቸው የሚያግዙ የተወሰኑ የታዳጊ ቡድኖችን ይለዩ።

# የበጎ ፈቃደኞች መሰረታዊ መመሪያዎች

ለበጎ ፈቃደኝነት፣ ለደህንነት፣ ለቡድን ገንዘብ አያያዝ፣ ለካምፖች እና ለሌሎችም የእርስዎ መመሪያ። ወደ Volunteer Toolkit ይሂዱ እና መርጃዎችን ጠቅ ያድርጉ። ወቅታዊውን የበጎ ፈቃደኞች መሰረታዊ መመሪያዎች በ GSCNC ድህረ ገጽ ላይ ቅጾች እና ሰነዶች ውስጥ ማግኘት ይችላሉ ወይም የታተመ ቅጂ ከአገልግሎት ክፍልዎ የእንግዳ አቀባበል ባለሙያ ወይም በመጀመሪያው የአገልግሎት ክፍል ስብሰባ ላይ ማግኘት ይችላሉ።

እንዲሁም እንደ ቡድን መሪ እርስዎን ለመርዳት የፕሮግራም መረጃን፣ ቡድን ማቋቋሚያ መመሪያ፣ የ Girl Scout እንቅስቃሴዎችን ለማቀድ መመሪያ፣ የግጭት አፈታት መረጃ እና ሌሎችንም ያካትታል!

- የ Girl Scouts **የልጆች-ለአዋቂዎች ጥምርታ፣** የተወሰነ ብዛት ያላቸው Girl Scouts ን ለመከታተል የሚያስፈልጉትን የአዋቂ በጎ ፈቃደኞች ቁጥር ያሳያል። እያንዳንዱ ቡድን ለልጆች ቢያንስ 12 ቦታዎች እና 9 የበጎ ፈቃደኛ ሚናዎች አሉት።
- Girl Scout **ቡድን ውስጥ ቦታ አያያዝ የሚሰራው እንደሚከተለው ነው፡ በመጀመሪያ የተመዘገቡት፣ ቡድኑ ውስጥ መጀመሪያ ይገባሉ።** የቡድን መሪዎች ክፍት ቦታዎች ያሏቸው ቡድኖችን የሚቀላቀሉ ልጆች ቤተሰቦችን እንዲያነጋግሩ የሚያሳውቅ አውቶማቲክ ኢሜይል ይደርሳቸዋል። ክፍት ቦታ ያላቸው ቡድኖች ማንኛውም የተመዘገበች ወይም በቡድኑ አደራጅ የተመደበችን ልጅ መቀበል አለባቸው።
- ልጆች የፕሮግራም ደረጃዎችን ሲቀይሩ ወይም ተጨማሪ የቡድን መሪዎች ወደ ቡድኑ ኮሚቴ ሲጨመሩ **ቡድኑ መያዝ የሚችለው ቁጥር ሊጨምር ይችላል።**
- **ገንዘብ የሚያስገኙ ዝግጅቶች** አንድ ቡድን ለአንድ ልዩ ጉዞ ወይም ፕሮግራም እንዲውል ለሚያስገባው የምርት ፕሮግራም ገቢ ማሟያ ካስፈለገው፣ ወጪውን ለማገዝ ፈቃድ ማግኘት እና ገንዘብ የሚያስገኝ ዝግጅት ማቀድ ይችላል። ዝግጅቱ በቡድኑ የሚደራጅ፣ በአገልግሎት ክፍሉ የሚጸድቅ እና በ Girl Scouts ታቅዶ የሚካሄድ ይሆናል (ከአዋቂ በጎ ፈቃደኞች ጋር በመተባበር)
- **የፍተሻ ነጥቦች እና የተከለከሉ ተግባራት።** ከ Girl Scouts ጋር ለማንኛውም እንቅስቃሴ በሚዘጋጁበት ጊዜ ለታቀደው እንቅስቃሴ ልዩ የደህንነት መመሪያዎችን ለማወቅ የደህንነት እንቅስቃሴ ፍተሻ ነጥቦችን መመሪያ በመከለስ ይጀምሩ።




# ተጨማሪ የGirl Scout ፕሮግራም አዘገጃጀት መርጃዎች

## በመስመር ላይ የሚገኘው የ EVENTS (ዝግጅቶች) የቀን መቁጠሪያ

በፕሮግራም ዝግጅቶች የቡደን ተሞክሮዎን ያበለጽጉ! ከምንታወቅባቸው ዝግጅቶች (እንደ የ Girl Scout ቀን Air & Space Museum ወይም የካምፕ ዋና ስራ አስፈፃሚ) አንስቶ እስከ በፕሮግራም አጋሮች የሚተዳደሩ አስደናቂ ፕሮግራሞች ድረስ፣ ለሁሉም የሚሆን ነገር አለ! gscnc.org ን ይጎብኙ እና 'አባላት' የሚለውን በመቀጠል 'ዝግጅቶች' የሚለውን ይጫኑ።

## Girl Scout Insider (Girl Scout ውስጥ አዋቂ)፡

ሊመዘገቡባቸው፣ ሊገኙባቸው ወይም ቡድኑን በሚመቸው ጊዜ ሊያዘጋጁቸው የሚችሏቸው የ Girl Scout ፕሮግራሞች ዝርዝርበዓመት ሁለት ጊዜ ኢሜይል ይላካል!

## የተሟሉ የፕሮግራም መርጃ ስብስቦች

የፕሮግራም መርጃ ስብስቦችን በመጠቀም የቡድን ስብሰባዎችን ወይም ዝግጅቶችን ከማቀድ ጭንቀት ይገላገሉ! የፕሮግራም መርጃ ስብስቦች አዝናኝ፣ እድሜን የሚመጥኑ መርጃዎች ሲሆኑ እንደ STEM፣ ጉዞዎች፣ ተፈጥሯዊ አካባቢ፣ የቡድን ስራ እና ጤናማ ኑሮን ለመሰላሉ የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ተዘጋጅተዋል። ለመሪዎች በትንሽ ወጪ በውሰት የሚገኝ እና ወደ የትኛውም ምክር ቤት ቢሮ ሊላክ የሚችል (አንዳንዶቹ ነጻ ናቸው)። ብዙ የመርጃ ስብስቦች Girl Scouts የእውቀና አርማዎችን እንዲያጠናቅቁ ይረዳሉ! ስለሚገኙ የመገልገያ ስብስቦች እና እንዴት አንድ ቦታ ማስያዝ እንደሚችሉ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ድህረ ገጻችንን www.gscnc.org/kits ይጎብኙ።

# ስለ ቡድን የገንዘብ አያያዝ መታወቅ ያለባቸው ሰባት ታላላቅ ነገሮች

**የቡድን ገንዘብ አስተዳዳሪ፡**

የቡድኑን ገንዘብ በየጊዜው ይቆጣጠራል እንዲሁም ሪፖርት ያደርጋል (የቡድን መሪ አይደለም!)

**የባንክ ሂሳብ - የGirl Scout የባንክ ሂሳብ ከሶስት ፊርማዎች ጋር**

በአገልግሎት ክፍል ገንዘብ አስተዳዳሪ፣ በቡድን ገንዘብ አስተዳዳሪ እና በቡድን መሪ በጋራ የሚከፈት የምክር ቤቱን የፌዴራል ታክስ መለያን የሚጠቀም።

ሁሉም ገንዘብ የቡድኑ እንጂ የግለሰብ አይደለም።

**የቡድን የመዋጮ ክፍያዎች**

የ Girl Scout ፕሮግራም ቁልፍ አካል የ Girl Scout ማለም፣ ሰርቶ ማግኘት፣ማድረግ ነው! የቡድን የመዋጮ ክፍያዎች ተመጣጣኝ መሆናቸውን ያረጋግጡ - በዓመት 25 ዶላር ይመከራል።

በቡድን ውስጥ ያሉ Girl Scouts በቡድኑ ውስጥ ምን ማድረግ እንደሚፈልጉ የሚያቅዱ ሲሆን፣ የቡድን በጎ ፈቃደኞች ደግሞ ልጆች ለ Fall Product እና ለ Cookie ፕሮግራሞች በጀት እና ግቦችን እንዲያወጡ ያግዛሉ።
አስፈላጊ ከሆነ፣ ለቡድኑ ጅማሬ ምን ያህል መዋጮ መደረግ እንዳለበት ይወስኑ።

**የ Girl Scout ስራ ፈጠራ ፕሮግራሞች - የ Fall Product እና Cookie ፕሮግራሞች**

Girl Scouts በ Fall Product እና በ Cookie ፕሮግራሞች ላይ ሲሳተፉ የቡድን ገቢ ያገኛሉ። Girl Scouts እንደ ቡድን በጋራ፣ የ Fall Product እና የ Cookie ገቢያቸው ምን ላይ እንደሚውል ይወስናሉ። ከቤት ውጪ የቆይታ ጉዞ ወጪን ከመሸፈን አንስቶ የአካባቢ አገልግሎት ፕሮጀክትን እስከ ማጠናቀቅ ድረስ፣ እነዚህ ፕሮግራሞች Girl Scouts እየተማሩ ገቢ ማግኘታቸውን ያረጋግጣሉ!

**ሪፖርት ማድረግ እና ደረሰኞች**

ቡድኖች በተጠየቀው መሰረት ሁሉንም የባንክ መግለጫዎች እና ደረሰኞች ለአገልግሎት ክፍል ገንዘብ አስተዳዳሪ መላክ አለባቸው።

**ከቀረጥ ነጻ መደረግ**

501 (c)3 ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት እንደመሆናችን፣ በጎ ፈቃደኞች ለቡድኑ ቁሳቁስ ሲገዙ ከቀረጥ ነጻ ማድረጊያ ቁጥራችንን ይጠቀማሉ።

**የገንዘብ እገዛ**

ለተመዘገቡ Girl Scouts እና የቡድን መሪዎች ለደንብ ልብስ፣ ለመጽሐፍ እና ለቡድን መዋጮ ክፍያዎች እገዛ ይገኛል። ቤተሰብ ማዋጣት ካልቻለ የቡድን መዋጮ ክፍያ ከፍተኛው መጠን በዓመት በአንድ Girl Scout 25 ዶላር ነው።

እንደ ጉዞ ወይም ልዩ ፕሮግራም ያሉ የተወሰኑ ተግባራትን ለመሸፈን የፕሮግራም ድጎማዎች ተዘጋጅተዋል። ዝርዝር በጀቶች እና/ወይም የጊዜ ሰሌዳዎች ያስፈልጋሉ።

ክፍያ መፈጸም ባለበት ወቅት ለብቁ የ Girl Scout ወጪ መሸፈኛ ገንዘብ በማይገኝበት ጊዜ የቡድን፣ የጋራ ወይም የግለሰብ ፕሮግራም ብድሮችን መጠየቅ ይቻላል። በበጎ አድራጊዎች ለጋስነት፣ ቡድኖች ለሚገለገሉባቸው የድር ጣብያ ላይ መድረኮች የገንዘብ ድጋፍ ይቀርባል። ለእያንዳንዱ የተዘ ጋጀ የገንዘብ እገዛ እንዴት ማመልከት እንደሚቻል የበለጠ መረጃ እና ዝርዝር መመሪያዎችን ለማግኘት ይህንን የገጽ አገናኝ https://form.jotform.com/GSCNCMembership/financial-assistance ይከተሉ።

# የገንዘብ አያያዝን በልጆች መሪነት ስር ማቆየት

የ Fall Product እና Cookie ፕሮግራም ገቢ ቡድንዎ ባስቀመጣቸው ግቦች ላይ በመመስረት ይለያያል።

**Girl Scouts እና የቡድኑ ኮሚቴ የቡድኑን በጀት ለማዘጋጀት እና ለመከተል በየዓመቱ በመተባበር ይሰራሉ።**

### ከዴይዚዎች እና ብራውኒዎች ጋር በጀት ማዘጋጀት፡

ቡድኑ ገንዘብ የሚያወጣባቸው አንዳንድ ነገሮች ምን እንደሆኑ (የስብሰባ አቅርቦቶች፣ የእውቅና አርማዎች፣ የሚቀጥለው ዓመት አባልነቶች) ከ Girl Scouts ጋር ይወያዩ።
ምን ማድረግ እንደሚፈልግ ቡድኑን ይጠይቁ።
የምርምር ስራዎችን ለቡድኑ ኮሚቴ አባላት ያከፋፍሉ። የተገኘውን ውጤት ለቡድኑ ያካፍሉ።
ቡድኑ ከታቀደው ገቢ ጋር የሚስማሙ ውሳኔዎችን እንዲወስን ይርዱት።

### ከጁንየሮች፣ ካዴቶች፣ ሲንየሮች፣ እና አምባሳደሮች ጋር በጀት ማውጣት፡

ቡድኑ ገንዘብ የሚያወጣባቸው አንዳንድ ነገሮች ምን እንደሆኑ (የስብሰባ አቅርቦቶች፣ የእውቅና አርማዎች፣ የሚቀጥለው ዓመት አባልነቶች) ከቡድኑ ጋር ይወያዩ።
በዚህ አመት እና በሚቀጥሉት ሁለት አመታት ውስጥ ምን ማድረግ እንደሚፈልግ ቡድኑን ይጠይቁ።
ህልሞቻቸው ምን ያህል እንደሚያስከፍሉ ግምት ማውጣት ላይ ይደግፏቸው።
ማግኘት በሚችሉት የገቢ አቅም ውስጥ ያሉ አማራጮች ላይ ያበረታቷቸው።
ቡድኑ እቅድ ሲኖረው፣ ለትልቅ ፕሮጀክት ወይም ጉዞ የተወሰነ ገንዘብ በየአመቱ መቆጠብ ሊጀምር ይችላል።

### የመጀመሪያው አመትዎ ላይ ባልተወሳሰበ ነገር ይጀምሩ!

ዴይዚዎች ተጨማሪ ገንዘብ በሚያስገኙ ተግባራት ላይ ላይሳተፉ ይችላሉ።

### ዴይዚ፣ ብራውኒ እና ጁኒየር ቡድኖች አመታዊ ገቢያቸውን የሚያወጡት በዚያው ዓመት ነው። ጉዞ እና የጉዞ እቅድ ቢያንስ በአንድ አመት ውስጥ መከናወን አለበት።

ገንዘብ ማግኘት ጊዜ ይወስዳል - ገንዘብ ለማግኘት ቢያንስ ከአንድ አመት በፊት ያቅዱ.

### Girl Scouts፣ ጠቅላላ የ Girl Scout ተሞክሯቸውን የገንዘብ ወጪ የሚሸፍኑት በ Fall Product እና በ Cookie ፕሮግራሞች ላይ በመሳተፍ ነው!

የሚቀጥለውን ዓመት አባልነቶች በበጀት ውስጥ ማካተትዎን እርግጠኛ ይሁኑ!

| ገቢ | በጀት | ትክክለኛ |
|---|---|---|
| የቡድን መዋጮ ክፍያዎች - በአንዲት ልጅ/25ዶላር | 300 ዶላር | |
| የ Fall Product ፕሮግራም | 150 ዶላር | |
| የ Cookie ፕሮግራም | 750 ዶላር | |
| **ጠቅላላ ገቢ** | **1200 ዶላር** | |
| **ወጪዎች** | **በጀት** | **ትክክለኛ** |
| የስብሰባ አቅርቦቶች (~2 ዶላር/ልጅ/ስብሰባ) | 384 ዶላር | |
| የእውቅና አርማዎች (3 ዶላር/የእውቅና አርማ፣ 10 የእውቅና አርማዎች/በልጅ) | 360 ዶላር | |
| ለቀጣዩ ዓመት አባልነት (25 ዶላር/አባል፣ 12 ሴት ልጆች እና 3 በጎ ፈቃደኞች) | 375 ዶላር | |
| የመስክ ጉዞ/ከቤት ውጪ የምግብ ማብሰያ | 50 ዶላር | |
| የአመቱ መጨረሻ ክብረ-በዓል | 30 ዶላር | |
| **ጠቅላላ ወጪዎች** | **1200 ዶላር** | |



ዓለምን የተሻለች ቦታ የሚያደርጉ፣ ወኔ፣ በራስ መተማመን እና መልካም ስነ-ምግባር ያላቸው ሴት ልጆችን በመገንባትዎ እናመሰግናለን!

girl scouts nation's capital